
በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ



# የአስር ቀን የአየር ሁኔታና ወርሃዊ

# የአየር ጠባይ

# ግምገማ ትንበያ መጽሔት

## ከኦገስት 21-31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

## እንዲሁም ከሰፕቴምበር 1-10፣11-20 2024

## የሚኖረው የአየር ሁኔታ  ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ሴፕቴምበር 2024

አዲስ አበባ

ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ርዕስ ገፅ


እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ....- 1 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ....- 3 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት ....- 3 -

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ....- 3 -

እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....- 4 -

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....- 5 -

እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....- 5 -

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....- 6 -

እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ....- 6 -

ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከሴፕቴምበር 1-10, 2024 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን ....- 8 -

ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከሴፕቴምበር 1-10, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ....- 8 -

እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ....- 8 -

ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11-20፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ....- 9 -

እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....- 10 -

እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....- 10 -




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት አሥራ አንድ ቀናት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች የተስፋፋ የደመና ሽፋንና ክምችት ነበራቸዉ፡፡ በተለይም በምዕራብና በመካከለኛዉ ኦሮሚያ፤ በምስራቅ እና ምዕራብ አማራ፤ በትግራይ፣ በአፋር ክልል፤ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል፤ በጋምቤላ ክልል ፤ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል፣ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፤ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል እና በሲዳማ ክልል፤ ሀረር እና ድሬዳዋ እንዲሁም በሰሜን የሱማሌ ክልል አከባቢዎች ላይ ከነበረው ጠንካራ እና የተስፋፋ የደመና ክምችት ጋር ተያይዘው በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል በመቀሌ 40፤ በነቀምት 52.3፤ በአዲስ አበባ 46.7፤ በአዲግራት 42.5፤ በአይደርመቆ 41፣ በአለም ከተማ 45፤ በአለምተፈሪ 41.2፤ በአምደወርቅ 48.8፤ በአንግርጉትን 40.6፣ 53.6፤ በአሶሳ 56.6፤ በአጽቢ 47፣ 74፤ በአየዉ 57፤ በቡለን 54.4፣ 84.6፤ በቡሬ 44.5፤ በቻግኒ 45፤ በዳሊፋጊ 54.2፤ በደባርቅ 42.5፤ በጋምቤላ 47.3፤ በወሊሶ 41.3፣ 42.8፤ በጉንዶመስቀል 57.2፤ በእምድብር 42.1፣ 41.1፤ በጂራ 51.4፤ በላሊበላ 47.4፤ በማይጨዉ 41.7፤ በመተማ 50.7፤ በአዳማ 41.3፤ ፤ በነጆ 63.4፤ በሰንቃጣ 47.8፤ በሻምቡ 41.7፣ 62.2፤ በሽሬ 42.2፤ በወላይታ ሶዶ 41.6 እንዲሁም በየትኖራ 40.0 ሚ.ሜ. የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል።

በአጠቃላይ ባለፉት ቀናት በ77 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለው የዝናብ መጠን ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 50.7-84.6 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ50 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካካል በቡለን፣ በአጽቢ፣ በነጆ፤ በሻምቡ፤ በጉንዶመስቀል፤ በአየሁ፤ በአሶሳ፤ በዳሊፋጊ፤ በአንገርጉትን፤ በነቀምት፤ በጂራ እና በመተማ ይጠቀሳሉ ፡፡

ባለፉት ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከትግራይ ክልል የምስራቅ፣ የማዕከላዊ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የደቡብ ምስራቅ እና ምዕራብ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


ዞኖች፤ ከአማራ ክልል አዊ፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፣ ዋግህምራ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ ሰሜን ሸዋ፣ ሰሜን፣ ደቡብ፣ ማዕከላዊ እና ምዕራብ ጎንደር፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ አሶሳ፣ ካማሺ እና የማኦ ኮሞ ልዩ ዞን፤ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሀረርጌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምስራቅ፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ)፣ አርሲ ፣ ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ቄለም ወለጋ፣ ጅማ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ ሀሪ እና ጋቢ ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል ሲቲ፣ ፋፋን እና ኤረር ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ እና ምስራቅ ጉራጌ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ስልጤ እና የየም ልዩ ዞን፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጋሞ፣ ጌዲኦ፣ ደቡብ ኦሞ እና ባስኬቶ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች እንድሁም ሀረር እና ድሬዳዋ ላይ ከ60-220 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ5-11 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸው (ካርታ 1 እና 2)፡፡ በተጨማሪም ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ኑዌር፣ አኝዋክ እና ማዣንግ ዞኖች፤ከአፋር ክልል አውሲ ዞን፤ ከኦሮሚያ ክልል ባሌ፣ ምዕራብ አርሲ እና ምስራቅ ሃረርጌ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሀላባ ዞን እንዲሁም ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ቡርጂ፣ ኮንሶ እና አማሮ ዞኖች ላይ ከ11-60 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ2-6 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸው፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር፤ ከትግራይ ክልል የምስራቅ፣ የማዕከላዊ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የደቡብ ምስራቅ እና ምዕራብ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል አዊ፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፣ ዋግህምራ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ ሰሜን ሸዋ፣ ሰሜን፣ ደቡብ፣ ማዕከላዊ እና ምዕራብ ጎንደር፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ አሶሳ፣ ካማሺ እና የማኦ ኮሞ ልዩ ዞን፤ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ ምስራቅ፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ(ሰላሌ)፣ አርሲ ፣ ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ቄለም ወለጋ፣ ጅማ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ ሀሪ፤ ጋቢ እና አውሲ ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል ሲቲ፣ ፋፋን እና ኤረር ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ እና ምስራቅ ጉራጌ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ ዞን ስልጤ እና የየም ልዩ ዞን፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጋሞ፣ ጌዲኦ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ባስኬቶ፣ ቡርጂ፣ ኮንሶ እና አማሮ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፣ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ኑዌር፣ አኝዋክ እና ማዣንግ ዞኖች  እንድሁም ሀረር እና ድሬዳዋ ላይ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ነበራቸው (ካርታ 3) ፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር

## እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


ባለፉት ቀናት የነበረው እርጥበት በተለያየ የእድገት ላይ ለሚገኙ የረጅም፣ የመካከለኛ እና የአጭር ጊዜ ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች፣ ለጓሮ አትክልቶችና ለፍራፍሬዎች የውሃ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በተለይም በምስራቅና በሰሜን ምስራቅ አካባቢዎች ለሚገኙት አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የመጠጥ ውሃ እና የግጦሽ ሳር አቅርቦት በተሻለ ሁኔታ እንዲኖራቸው ያስቻለ ነበር፡፡

በአንፃሩ በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከነበረው ከባድና ተከታታይነት ካለው እርጥበት ጋር ተያይዞ ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች የጎርፍ ክስተቶች፣ የመሬት አቀማመጣቸው ከፍተኛና ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች የመሬት መንሸራተት፣ መሰንጠቅና ናዳ እንዲሁም በሰብሎች ላይ የውሃ መተኛትና መጥለቅለቅ ሁኔታዎች ተከስተዋል፡፡

በተለይም በሰሜን ጎንደር ዞን በጠለምት፣ ጃናሞራ፣ አዲአርቃይ እና በየዳ ወረዳዎች፣ በሥልጤ ዞን ምስራቅ ስልጤ እና ስልጤ ወረዳዎች፣ በትግራይ ደቡባዊና ምስራቃዊ ዞን ጉሎ መህዳ ወረዳዎች፣ እንዲሁም በሰሜን ሸዋ ዞን ደብረሲና ወረዳ እና በተለያዩ የሀገራችን አካባቢዎች ላይ በደረሰው የመሬት መንሸራተት እና በደቡብ ወሎ ዞን ወረባቦ ወረዳ በነበረው ከባድና በረዶ የቀላቀለ ዝናብ በሰብሎች፣ በንብረትና በሰው ህይወት ላይ ጉዳት እንዳደረሰ ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች ያመለክታሉ (ካርታ 4)፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት በአባይ፣ ተከዜ፣ መረብጋሽ፣ ባሮ አኮቦ፣ አፋር ደናክል፣ አዋሽ እንዲሁም የላይኛውና የመካከለኛው ኦሞግቤ፤ ስምጥ ሸለቆ፣ ገናሌ ዳዋ እና የዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የእርጥበት መጠን አግኝተዋል፡፡ በተለይም የላይኛውና የመካከለኛው አባይ፣ የተከዜ፣ የኦሞጊቤ እና የስምጥሸለቆ ተፋሰሶች ላይ እጅግ በጣም ከፍተኛ የእርጥበት መጠን ነበራቸው፡፡ ይህም የእርጥበት ሁኔታ በየተፋሰሶቹ በሚገኙ ግድቦች፣ ሰው ሰራሽ የውሃ መያዥያዎች እንዲሁም የከርሰ ምድር እና የገጸ ምድር የውሃ አቅምን ከማጎልበት አንጻር ጥሩ አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ በአንፃሩ በአንዳንድ የሀገሪቱ ተፋሰሶቸ ላይ ከነበረው ከባድና ተከታታይነት ካለው እርጥበት ጋር ተያይዞ ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች የጎርፍ ክስተቶች እንዲሁም የግድቦች ከፍተኛ የውሃ ሙላት እንደነበራቸው የተሰበሰቡ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ (ካርታ 5)፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በመደበኛ ሁኔታ በሴፕቴምበር ወር የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ቀስ በቀስ ከምስራቅ እና ሰሜን ምስራቅ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ ከፍሎች ላይ እየተዳከሙ የሚሄድበት ወቅት ነው፡፡ በመሆኑም የክረምቱ ዝናብ በስርጭትም ሆነ በመጠን ከምስራቅ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቀስ በቀስ የመቀነስ አዝማሚያ የሚያሳይበት ጊዜ ነው፡፡

በመጪዎቹ የሴፕቴምበር የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች በተለይም በምዕራብ አጋማሽ እንዲሁም በመካከለኛው የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ በተለይም በመካካለኛው፣ በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ እንዲሁም በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ጠንካራ እና የተስፋፋ የዝናብ መጠንና ስርጭት እንደሚኖራቸው አሀዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 6)፡፡ በተጨማሪም ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች ላይ በመነሳት በመካከለኛው፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በምዕራብ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይኖረቸዋል (ካርታ 6)፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


በመሆኑም ከባለፉት የክረምት ወራት ጀምሮ ከመደበኛ በላይ ዝናብ የነበረ ሲሆን፤ በሚቀጥሉት ቀናትም ከመደበኛ በላይ የዝናብ መጠንና ስርጭት የሚኖር ሲሆን ይህም ሁኔታ የጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አከባቢዎች ላይ ተጽዕኖ እንዳይደርስ አስፈላጊዉን ቅድመ ጥንቃቄና ዝግጅት ማድረግ እንደሚያስፈልግ የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ይጠቁማል (ካርታ 6 እና 7) ፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ምስራቅ፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ)፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ሆሮጉዱሩ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ጅማ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፤ አዲስ አበባ፤ ከአማራ ክልል ሰሜን፣ ደቡብ፣ ማዕከላዊ እና ምዕራብ ጎንደር፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ ሰሜን ሸዋ፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን እና ዋህግምራ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ አሶሳ፣ ካማሺ እና የማኦኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ኑዌር፣ አኝዋክ እና ማዣንግ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ስልጤ፣ ጉራጌ እና ምዕራብ ጉራጌ፣ የቀበና፣ የጠምባሮ እና የማረቆ ልዩ ወረዳ፣ ሀላባ፣ ሀዲያ እንዲሁም የየም ልዩ ዞን፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌዲኦ እና ወላይታ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤ ሁሉም የሲዳማ ክልል ዞኖች፤  ከትግራይ ክልል የምስራቅ፣ የደቡብ ምስራቅ፣ የማዕከላዊ፣ የሰሜን ምዕራብ እና የምዕራብ ዞኖች እንዲሁም ሀረር እና ድሬዳዋ ላይ በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6  እና 7)፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ በፀኃይ ሀይል ታግዞ ከሚፈጠሩ  ደመና ክምችት ጋር ተያይዞ ነጎድጓዳማ ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡


በሌላ በኩል ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት ከኦሮሚያ ክልል ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፤ ቦረና፣ ጉጂ ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ከአፋር ክልል ቅልበቲ እና አውሲ ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል ሲቲ፣ ፋፋን፣ ኤረር፣ ጀረር፣ ኖጎብ፣ ሊበን እና ዳዋ ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንሶ፣ አማሮ፣ ባስኬቶ፣ ቡርጂ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6) ፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713  ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከሴፕቴምበር 1-10, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከሴፕቴምበር 1-10, 2024 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን

## እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ


በመደበኛ ሁኔታ በሴፕቴምበር ሁለተኛው አሥር ቀናት የክረምት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከሰሜንና ከሰሜን ምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች እየተዳከሙ የሚሄዱበትና ከዚህም ጋር ተያይዞ የወቅቱ ዝናብ በመጠንም ሆነ በሥርጭት በኀላ መልኩ እየቀነሰ ይሄዳሉ፡፡ በሌላ በኩል የክረምት ዝናብ ድንበር (ITCZ) ወደ ምዕራባዊው አጋማሽና ወደ ደቡባዊው የኢትዮጵያ ክፍሎች ስለሚያፈገፍግ ዝናቡ በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ ቀጣይነት የሚኖረው ሲሆን፤ በተመሳሳይ ሁኔታም የደቡብ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ሁለተኛውን የዝናብ ወቅታቸውን ቀስ በቀስ ማግኘት ይጀምራሉ፡፡

በሚቀጥሉት የሴፕቴምበር ሁለተኛው አሥር ቀናት አሁን ከሚታዩትና በቀጣይነትም ከተተነበዩት የትንበያ መረጃዎች መረዳት እንደተቻለው ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቀጣይነት ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም፤ በሰሜን ምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ እንዲሁም በመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 8)፡፡ በተጨማሪም በፀኃይ ሀይል ታግዞ ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች ጋር ተያይዞ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በአንዳንድ ስፍራዎች ላይ አልፎ አልፎ በረዶ የቀላቀለ ከባድ ዝናብ እንደሚኖር አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 8)፡፡ በተጨማሪም በዚህ ጊዜ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ከቀን ወደ ቀን የደመና ሽፋን እየጨመረ የሚሄድ ሲሆንና ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ (ካርታ 8) ፡፡




ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11-20፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የሴፕቴምበር የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት የመኸር አብቃይ በሆኑት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ እንደሚኖራቸው ከመጠበቁ ጋር ተያይዞ በቀጣይ ለሚያከናውኑት የግብርና እንቅስቃሴ አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡ በተለይም በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙም ሆነ ፍሬ በመሙላት ላይ ላሉ የመኸር ሰብሎች እንዲሁም ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም የወቅቱ ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ዉሃ አቅርቦትን ከማሻሻሉም በተጨማሪ የዝናብ ውሃን ለመሰብሰብና ለማጠራቀም ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ በሌላ በኩል በአንዳንድ ቦታዎች ከመደበኛ በላይ ዝናብ በሚጠበቅባቸዉ እና ተደጋጋሚ የሆነ የእርጥበት ሁኔታ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ቦታዎች ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊከሰት ስለሚችል ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑና በውኃ መብዛት በሚጠቁ ቦታዎች አርሶ አደሩ እና የሚመለከታቸው አካላት በጋራ በመሆን የበዛውን ውሃ ከማሳ በማስወገድ እና በማንጣፊፍ የጎርፍ ውሃ መቀልበሻ ቦዮችን ከወዲሁ በማዘጋጀት በሰብሎች፣ በእንስሳትና በንብረት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል። በተጨማሪም ከሰብል ጥበቃ አንፃርም ከእርጥበት መብዛት ጋር የአረም መከሰትና  የሰብል ተባይም ሆነ በሽታ ለመከሰት አመቺ ሁኔታን ሊፈጥር ስለሚችል የሚመለከታቸዉ አካላትና አርሶ አደሮች የማሳ ጉብኝት በየጊዜው በማድረግ አረምን በወቅቱ በማረም ፀረ-አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን በመጠቀምና በወቅቱ ከግብርና ባለሙያ በሚያገኙት ምክረ ሀሳብ በመደገፍ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ቀናት በአባይ፣ ተከዜ፣ ባሮ አኮቦ፣ የላይኛው እና መካከለኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛው ገናሌ ዳዋ እና ዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ ይኖራቸዋል፡፡ በተጨማሪም በታችኛው አዋሽ እና አፋር ደናክል ተፋሰሶች መጠነኛ እርጥበት



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ያገኛሉ፡፡ ይህም ሁኔታ የውሃ ሀብት ግብዓትን ከማጎልበትም በተጨማሪ በቀሪዎቹ ቀናት ውሃን መያዝ ለሚፈልጉ ግድቦች ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በሌላ በኩል ከሚኖረው ከፍተኛ እርጥበት ጋር ተያይዞ ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ ተፋሰሶችና ላይ ንዑስ ተፋሰሶች ላይ የጎርፍ ክስተት የማስከተል አሉታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል፡፡ ይሁን እንጂ ከፍተኛ የውሃ መጠን ባላቸው ግድቦች ማለትም በተከዜ፣ በተንዳሆ፣ በቀሰም፣ በጣና በለሥ እና በርብ ግድቦች ላይ በቀጣይ የሚኖረው እርጥበት ተጽዕኖ እንዳያደርስ  በግድቦቹ የውሃ መጠን ላይ የቅርብ ክትትል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et